# የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ
## COMMERCIAL BANK OF ETHIOPIA

### <u>የጨረታ ማስታወቂያ</u>
### <u>ያገለገሉ ንብረቶች ጨረታ ቁጥር 001/2024/25</u>

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በጥገና ጊዜ የተቀየረ የተሽከርካሪ ዘይት ባለበት ሁኔታ በጨረታ አወዳድሮ በሽያጭ ለማስወገድ ይፈልጋል፡፡

1. ስለ አሻሻጡ የተዘጋጀውን ዝርዝር ሁኔታ የያዘውን ሰነድ ቄራ ፊት ለፊት በሚገኘው የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ሕንፃ 2ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 211 የማይመለስ ብር 300.00 (ሦስት መቶ ብር ብቻ) በመክፈል ከሐምሌ 25 ቀን 2016 ዓ.ም. ጀምሮ እስከ ነሐሴ 15 ቀን 2016 ዓ.ም ከጠዋቱ 2:00 ሰዓት እስከ ቀኑ 10:00 ሰዓት ድረስ ባሉት የስራ ቀናት መውሰድ ይችላሉ፡፡

2. ተጫራች በጥገና ጊዜ የተቀየረ የተሽከርካሪ ዘይት ከሐምሌ 25 ቀን 2016 ዓ.ም. ጀምሮ እስከ ነሐሴ 16 ቀን 2016 ዓ.ም ድረስ ቃሊቲ ከመንገድ ትራንስፖርት የማሽከርከር ብቃት ማረጋገጫ እና ማሰልጠኛ ተቋም አለፍ ብሎ በሚገኘው የባንኩ የተሽከርካሪ ጋራዥ /የቀድሞ አማልጋ ሜትድ/ ግቢ ውስጥ ከጠዋቱ ከ2:00 ሰዓት እስከ ቀኑ 6:00 ሰዓት ከሰዓት በኋላ ከቀኑ 7:00 ሰዓት እስከ ቀኑ 10:00 ሰዓት ድረስ ባሉት የስራ ቀናት በመገኘት ማየት ይችላል፡፡

3. በጥገና ጊዜ የተቀየረ የተሽከርካሪ ዘይት ለሚጫረቱ ተሳታፊዎች ከሚመለከተው የመንግሥት አካል የማስወገድ ፍቃድ ያለውና የፍቃዱ ወረቀት ወይም ሰርተፊኬት ዋናውን (Original) እና አንድ ቅጅ (Copy) ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

4. ተጫራች የጨረታ መነሻ ዋጋውን 25% (ሃያ አምስት በመቶ) የጨረታ ማስከበሪያ (Bid Bond) በባንክ ክፍያ ማዘዣ (CPO) <u>ለኢትዮጵያ ንግድ ባንክ</u> (Commercial Bank of Ethiopia) በሚል ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

5. የተዘጋጀው የጨረታ ሰነድ ማስገቢያ ሳጥን ነሐሴ 17 ቀን 2016 ዓ.ም ከጠዋቱ 3:00 ሰዓት ላይ ታዛቢዎች በተገኙበት ይታሸጋል፡፡

6. ተጫራች የሚሰጠውን ዋጋ ከጨረታ ሰነዱ ላይ ባለው ክፍት ቦታ በመሙላት የጨረታ ማስከበሪያ እና ሌሎችም አስፈላጊ ሠነዶችን በፖስታ በማሸግ ቄራ ፊት ለፊት በሚገኘው የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ሕንፃ 2ኛ ፎቅ በተዘጋጀው የጨረታ ሰነድ ማስገቢያ ሳጥን ውስጥ ነሐሴ 17 ቀን 2016 ዓ.ም ከጠዋቱ 3:00 ሰዓት እስከ 4:00 ሰዓት ብቻ ያስገባል፡፡

7. ነሐሴ 17 ቀን 2016 ዓ.ም ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው እንዲሁም ታዛቢዎች በተገኙበት ቄራ ፊት ለፊት በሚገኘው የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የሠራተኞች የመዝናኛ ክበብ አዳራሽ በግልጽ ይከፈታል፡፡

8. ለጨረታ ማስከበሪያ የተያዘው ገንዘብ አሸናፊ ለሚሆነው በሚገዛው ንብረት ክፍያ ላይ የሚታሰብ ሲሆን አሸናፊ ላልሆኑት ለጨረታ ማስከበሪያ ያስያዙት ገንዘብ ተመላሽ ይደረግላቸዋል፡፡

<u>ባንኩ የተሻለ አማራጭ ካገኘ ጨረታውን በከፊልም ሆነ በሙሉ የመሠረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡</u>